# በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት

## የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የ2014 በጀት ዓመት እቅድ ላይ የተሰጠ

## ግብረ-መልስ

ታህሳስ 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# 1.መግቢያ

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በህገ መንግሥቱ አንቀፅ 55 ንዑስ አንቀፅ 17 በተሠጠዉ ስልጣንና ሀላፊነት እንዲሁም በህ/ተ/ም/ቤት በተሻሻለው የአሠራርና የአባላት ስነ ምግባር ደንብ ቁጥር*6/2008* ዓ.ም የሚከታተለቸው የአስፈፃሚውን መስሪያ ቤቶችን ዓመታዊ ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ተቀብሎ የመመርመር እና በመስክ ምልከታው ክትትል፤ ቁጥጥርና ድጋፍ በማድረግ አስፈላጊዉን ግብረ-መልስ የመስጠት ስልጣን ተሰጥቶታል። በዚሁ መሰረት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ያዘጋጀውን የ2014 በጀት ዓመት መነሻ ዕቅድ በመገምገም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችንና በጥንካሬና በድክመት የተለዩትን እንዲሁም በእቅዱ ቅርፅና ይዘት ላይ በባለሙያ በግምገማ ከተሰጠው አስተያየት በተጨማሪ በፊት ለፊት መድረክ ላይ ከምክር ቤት አባላት ለተቋሙ የቀረቡ አንኳር አንኳር አስተያየቶችንና የተሰጡ ቀጣይ አቅጣጫዎችን በማከል ለተሰጡት ግብረ-መልሶች እንደ አንድ መነሻ ግብአት በመጠቀም እንደሚከተለው ግብረ-መልስ ተሰጥቷል።

## በጥንካሬ የታዩ

1. የእቅዱ ዋና ዋና ሃሳቦች /executive summary/ ጠቅለል ተደርገው መጀመሪያ መግቢያው ላይ መቀመጡ፣
2. የቀረበው እቅድ ሶስት የትኩረት መስኮችን፣ አምስት የትኩረት አቅጣጫዎችን፣ አስቻይ ሁኔታዎችን፣ የዕቅዱ ማስፈፀሚያ ስልቶችን፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችንና የመፍትሄ ሃሳቦችን፣ ዋና ዋና ግቦችን፣ የግብ አመላካቾችን፣ መድረሻ ኢላማዎችን፣ የኮሚሽኑን የበጀት እቅድ፣ የክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ አሠጣጥ ሥርዓትን፣ ተልዕኮውን በብቃት መወጣት እንዲችል የአስር ዓመት መሪ አቅድና የአምስት አመቱን ስትራቴጂክ የልማት ዕቅድ እንዲሁም እንደ መነሻ የ2013 የዕቅድ አፈፃፀምን በመዳሰስ የተዘጋጀ መሆኑ፣
3. በሁሉም አካባቢዎች የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ለመሳብ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ያለ ሲሆን ከውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰት በ2013 የዕቅድ ዘመን ከነበረው 3.97 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በመነሳት በ2014 በጀት ዓመት 5.13 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር

ለማድረስና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት ድርሻ በአማካይ በ7 በመቶ ለማሳደግ መታቀዱ የሚያበረታታ መሆኑ፣

4. የኢንቨስትመንት መረጃዎችን በተለያዩ ዘዴዎች መረጃ ለማሰራጨት የፍቃድ፣ ምዝገባ እና የማበረታቻ አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ በonline ለማድረግ፣ የሰራተኛውን የመፈጸም አቅም እንዲጎለብት በሃገር ውስጥና በውጭ ሀገር ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና ሰራተኛው እንዲያገኝ መታቀዱ፣
5. በግቡ ላይ ይደረስበታል ተብሎ የተቀመጡት ኢላማዎች ሊለካ በሚችል በቁጥርና በፐርሰንት ተለክተው መቀመጣቸው፣

6. ኮሚሽኑ የበጀት አመቱን እቅድ ለመፈፀም 4 ፕሮግራሞችን ያዋቀረ ሲሆን በአራቱም ፕሮግራሞች በዋና ዋና ተግባራት ስር በጀት ተደልድሎ መዘጋጀቱ፣

7. የኢንቨስትመንት ዘርፉን ለማበረታታት እንዲቻል በግብርና ስራ መስኮች ላይ፣ አግሮ-ፕሮሰሲንግ እና የቆዳ ምርቶች ላይ፣ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችንና ከፊል ግብዓቶችን በማምረት የማኑፋክቸሪንግ የእሴት ሰንሰለት ለማጠናከር፣ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ አምራቾችን ለመደገፍ፣ በአገልግሎት ዘርፍ በተለይም በቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዘርፍ ላይ በማተኮር በአገር በቀል የኢኮኖሚክ ሪፎርም ላይ በትኩረት የተለዩ ተግባራትን ለማከናወን መታቀዱ፣
8. ከፍተኛ አቅም፣ ጥሩ ስምና ዝና ያላቸውን የውጭ ባለሃብቶችንና ኩባንያዎች በመለየትና በጥንቃቄ በመመልመል በተለይም ኤክስፖርት-ተኮር እና ለዜጎች ሰፊ የስራ ዕድል ሊፈጥሩ በሚችሉ የማኑፋክቸሪንግና ኮንስትራክሽን ዘርፎች ላይ እንዲሠማሩ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ ትኩረት የተሰጠው መሆኑ፣
9. የኮሚሽኑ የበጀት ዓመቱ የልማት ዕቅድ አጠቃላይ አፈጻጸሙ ውጤታማ እንዲሆን በፕላን ኮሚሽን በተዘጋጀው የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት አቀራረብ ስርአት መሰረት የተቀመጡ ዒላማዎችንና ግቦችን ማዕከል በማድረግ የቀረበ ሲሆን በተጠናከረ የክትትልና ግምገማ አሰራር መሰረት ለመገምገምና ስራዎችን ወጥነት ባለው አሰራር ለማከናወን እንዲረዳ እቅዱ የተዘጋጀ መሆኑ፣

## በእጥረት የታዩ

1. ከታቀደው እቅድ የሚጠበቅ የግብ ውጤት አለመገለፁ፣
2. በፕሮግራም በጀት አሰራር መሰረት የመደበኛና ካፒታል በጀት ወጪዎችን ለማቀናጀት እንዲቻል የበጀቱ ምንጭ ተገልጾ በተለያየ ፎርማት በጀቱ ተዘጋጅቶ አለመቅረቡ፣
3. የቀረበው የፕሮግራም በጀት ዕቅድ በየሩብ አመቱ ተከፋፍሎ አለመቅረቡ፣
4. እቅዱ አራቱን እይታዎች ከነክብደታቸው አካቶ በቢኤስ ሲ እስታንዳርድ ልክ ተሰርቶ አለመቅረቡ፣
5. እቅዱ በዝግጅት ምዕራፍ፣ በተግባር ምዕራፍ እና በማጠቃለያ ምዕራፍ ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት ተለይተው አለመታቀዳቸው፣
6. ግብ 6 ላይ ለተገለፁት 13 የመንግስት፣ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሙሉ ለሙሉ ወደ ስራ እንዲገቡ በማድረግ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ማከናወን ለሚለው ከታች ግቡን ለማሳካት ይከናወናሉ ተብለው የተቀመጡት ዋና ዋና ተግባራት በይዘታቸው የግቡ ገላጭ አለመሆናቸው፣
7. የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ማለትም የሴቶችና ወጣቶችን አካታችነት፣ በተለያዩ ችግር ውስጥ የሚገኙ ወገኖችና ወላጅ አልባ ለሆኑ ህጻናት ድጋፍ ለማድረግ እንዲቻል ለዚሁ ማስፈፀሚያ ራሱን ችሎ ለስርአተ ፆታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ፕሮግራም ከሌሎቹ የበጀት ስርአቶች ጋር ተዘጋጅቶ አለመቅረቡ፣

## ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊካተቱ የሚገባቸው ጉዳዮች፤

1. በኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ የመልካም አስተዳደር ችግር የሚታይበት በመሆኑ ጉዳዩ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶት ለመስራት እንዲቻል በእቅዱ ውስጥ የመልካም አስተዳደር ዋና ዋና ቁልፍ ተግባራት መካተት አለባቸው፣
2. ሁሉም የመንግስትና የግል ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሙሉ ለሙሉ ወደ ስራ እንዲገቡ ለማድረግ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶት ከፍተኛ የክትትልና የድጋፍ ስራዎች መሰራት ይኖርበታል፣
3. በአሁኑ ሰአት የውጪ ሚዲያዎች በሃገራችን የውስጥ ጉዳይ ላይ እያደረጉት ያለው አሉታዊ ተፅእኖ፣ በሀገራችን ላይ የተጋረጠው ጦርነቱ ያመጣው ቀውስና የሰላም

ማጣት ችግር፣ አገራችን ከአጎዋ የንግድ ትስስር እንድትወጣ መደረጉ፣ በዘላቂነት ኢንቨስትመንቱ እንደነዚህ አይነቶች ተግዳሮቶችን ተቋቁሞ ማለፍ እንዲችልና በቀጣይ ለችግሮች የማይበገር የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲኖር ተቋሙ የመፍትሄ አቅጣጫዎቹን በእቅዱ ውስጥ በአግባቡ ለይቶ ማስቀመጥ ይኖርበታል፣

4. ሃገራችንን ከተፈታተኗትና ወደ ኃላ ካስቀሯት ነገሮች አንዱ ሙስና ወይም ሌብነት ነው:: ስለሆነም በኢንቨስትመንቱ ውስጥ እየተስተዋለ ያለውን መዋቅራዊ ሌብነት ለመቅረፍ መወሰድ የሚገባቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች በእቅዱ ውስጥ በግልፅ ተመላካቶ መቀመጥ ይኖርበታል፣
5. በኮሚሽኑ ተልእኮ ላይ "ጥራት ያለው ኢንቨስትመንትን በመሳብ እና ቀጣይነቱን በማረጋገጥ የምጣኔ ሃብት፣ የሥራ ዕድል፣ የወጪ ንግድ ገቢን ማሳደግና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ" የሚለው ተካቶ የእቅዱ አካል ማድረግ፣
6. ከኢነቨስትመንቱ ጋር ተያይዞ በጦርነት የወደሙ ኢንዱስትሪዎች፣ ፋብሪካዎችና ሌሎች መሰረተ ልማቶች ወደ ነበሩበት ለመመለስ እንዲቻል በዚህ ጉዳይ ላይ ሀገራችን አሁን ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ በመዳሰስ ቀጣዩ የትኩረት አቅጣጫዎቹ ምን ለመስራት እንደታቀደ በእቅዱ ውስጥ ተካቶ መቅረብ ይኖርበታል፣
7. የኢንቨስተመንት ከበባዊ ሁኔታን (Ease of Doing Business) በተመለከተ በፌደራል ደረጃ ጥሩ እንቅስቃሴ እየታየ ያለ ቢሆንም እስከ ታችኛው እስከ ክልል ድረስ ወርዶ በኢኮኖሚው ላይ ምን አይነት ፋይዳ እንዳመጣና አጀንዳው በስራ ላይ ስለመዋሉ ኮሚሽኑ ለክልሎች የአቅም ግንባታ በመስጠት በቀጣይ ከክልሎች ጋር በቅንጅት ለመሥራት ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል፣
8. በቀጣይ የተቋሙ ቁልፍ ተግባራትና ቁልፍ ችግሮች በአግባቡ ተለይተው መቅረብ ይኖርባቸዋል፣
9. የስራ መርሃ ግብሩን እቅድ አራቱን እይታዎችን (የተገልጋይ እይታ፣ በጀት፣ የውስጥ አሰራር እይታ፣ መማማርና ዕድገት) ለይቶ እንደ ሀገር በውጤት ተኮር የአሰራር ስርዓት መመሪያ መሰረት ፎርማቱን ጠብቆ ማዘጋጀት፣
10. በ3ቱ የአመራር ኡደቶች (ሂደቶች) ማለትም በዝግጅት ምዕራፍ፣ በተግባር ምዕራፍ እና በማጠቃለያ ምዕራፍ ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራት ተለይተውና ተከፋፍለው መቅረብ ይኖርባቸዋል፣

11. የቀረበው የፕሮግራም በጀት ለክትትልና ቁጥጥር እንዲያመች የበጀት አስተቃቀድ ስርአት ባለው መንገድ በየሩብ አመቱ ተከፋፍሎ መቅረብ አለበት፣
12. በእቅዱ ወስጥ የቀረቡት ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በቅንጅት እየሰሩ ያሉ ባለ ድርሻ አካላት ወይም አጋር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች አቀራረባቸውና ስያሜአቸው በቀድሞው አጠራር በመሆኑ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው የፌዴራል ተቋማት ማሻሻያ አዋጅ መሰረት ስማቸው በአዲሱ ስያሜ ተለይቶ ቢቀርብ፣
13. ኢትዮጵያ የያዘችው ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋምና ዝቅተኛ የካርበን ልቀት መጠን እንዲኖር ለማድረግ የተፈጥሮ ሀብትንና የአካባቢ ጥበቃን ከመንከባከብና ተጠቃሚ ከመሆን በተጨማሪ ለብክለት ከሚዳርጉ ነገሮች ለመጠበቅ እንዲቻል ስትራቴጂው በኢንዱስትሪ ፓርኮች አካባቢ በዘላቂነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሰራ ጥረት መደረግ አለበት፣
14. በአሁኑ ሰዓት በአገራችን የተከሰተው የሠላም ማጣት ችግር በኢንቨስትመንት ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተጽእኖ ከፍተኛ በመሆኑ በጦርነቱ ምክንያት የወደሙ የኢንዱስትሪ ተቋማትን ወደነበሩበት ለመመለስ እንዲቻል ከሌሎች አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት መፍትሔ ይሆናሉ ተብለው የተቀመጡ አቅጣጫዎች በእቅዱ ላይ ተመላክተው ቢቀርቡ፣

## ማጠቃለያ

ቋሚ ኮሚቴው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የላከውን የ2014 በጀት አመት እቅድ ከ5 አመቱ ስትራቴጂክ እቅድ ጋር በማነፃፀር፣ በፊት ለፊት መድረክ ለተጠሪው ተቋም ከአባላት የቀረቡ ተገቢ የሆኑ አስተያየቶችን በማካተት፣ የእቅዱን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመገምገም እንዲሁም በዕቅዱ ውስጥ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊካተቱ የሚገባቸው ጉዳዮችን በመለየት መ/ቤቱ እነዚህን ከላይ የቀረቡትን አስተያየቶች በግብአትነት በመጠቀም እቅዱን እንደገና አሻሽሎና አስተካክሎ እንዲልክልን ቋሚ ኮሚቴው ይህንን ግብረ መልስ ሰጥቷል፡፡